ዋሽንግቶን; October 10, 2019

# ከዓልም አቀፍ የዓማራ ህብረት የተሰጠ መግለጫ

**" ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ሲወርዱ እኛ ክፍብለን እንታይ "**

በቅድስት ሃገር ኢትዮጵያ የዘር ፖለቲካ ከፍተኛው ደርጃ ላይ ደርሷል። በ1992 ዓ. ም. 'ሊዮን ሙገሴራ' (Leon Mugesera) የተባለ የሁቱ ፓርቲ ክፍተኛ አመራር ደጋፊዎቹን ሲሰብክ ቱትሲ የተባልውን ጎሳ 'cockroach ' ወይም 'በረሮዎች' ስለሆኑ ወደ መጡበት ኢትዮጵያ መልሷቸው እያለ ደጋፊዎቹን ይሰብክ ነበር። በዚህ ፀያፍ ንግግር የተቀሰቀሱና የተገፋፉ 'ሁቱዎች' ቱትሲዎችን በግፍና በሚዘገንን ሁኔት ጨፈጨፏቸው። በሶስት ወር ጊዜ (100 days) አንድ ሚሊዮን ትሲዎች ታረዱ። በናዚ የጀምረው የዘር ማጽዳት በሩዋንዳ መሬት በአፍሪካ አሃጉር ታሪክ ራሷን ደገመች። የዓለም ማህበረሰብ በተለይ የተባብሩት መንግስታት በዝምታ አለፈው። ሁለቱ የሃኛው ክፍለ ዘመን ዘግናኝ የዘር እልቂቶች ዓለምን ክፉኛ አሳዘኑ። ሥልጡኑ የዓለም ማህበረሰብ ከእንስሳ ያልተሻለ እንደሆነ ታየ።

በኢትዮጵያም የዘር ፖለቲካ ላለፉት ሰላሳ ዓመታት በረቀቀ ዘዴ ሲሰብክ ቆይቷል። የሃገራችን የዘር ፖለቲካ ከርዋንዳውና ከናዚ ጀርመኑ በዓይነቱና በይዘቱ ይለያል። በኢትዮጵያ የዘር ፖለቲካ እንደጥሩ የፖለቲካ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያው ስርዓት ተወስዶ በሕገ መንግስት ተደንገጓል። በመንግሥት መስሪያ ቤት የሥራ መመሪያ ወጦለት እየተከናወነ ይገኛል። ይህ ብልሹ ሕገ መንግስት ዓማራን ነጥሎ በማጥቃት ከፖለቲካዊ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አሰራሮችና መርሃ ግብሮች ለማስወገድ አልሟል። የዓማርን ዘር ከምድረገጽ ለማጥፋት በመመምሪያና በመንግሥት ትእዛዝ በግሃድ የሕግ ሽፋን ተሰጦት መካሄዱ የችግሩን አሳሳቢነት ፍንትው አርጎ ያሳያል።

ይህ አካሄድ አደገኛ ብቻ ሳይሆን በዘር ፖለቲካ ለሰከሩ ልሂቃንና ብድኖች ሕጋዊ ሰውነትና ሽፋን የሚሰጥ ሆኖ አግኝተነዋል። እንደ ጃዋር ሞሃመድ፤ ፕሮፌሰር ሕዝቂል ገቢሳ፤ አቶ በቀል ገርባ የመሳሰሉት በዘር ፖለቲካ በሰከሩ፤ የዘር ፖለቲካ አራማጆችና ሰባኪዎች አማራ ጠል ትርክታቸውን በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች በመስበክ፤ በመቀስቀስና በማስተማር ላይ ናቸው። እነዚህ ዘረኞች ከርዋንዳው ራዲዮ ሚሌ በቀሰሙት ልምድ ተመስርተው OMN የተባለ ራዲዮ ጣቢያ ከፍተው በዓማራው ሕዝብ ላይ የሃሰት ትርክትና ፀረ ዓማራ ዘመቻቸውን ተያይዘውታል።

ጽንፈኞችን በዝምታና በቸልተኝነት ማለፍ የሩዋንዳው ጭፍጨፋ በአማራ ላይ እንዲካሄድ እንደመፍቀድ ይቆጠራል። እዚህ ላይ ቀዳማዊ ሃይለ ስላሴ "ከታሪክ የተማርነው ቢኖር የማድረግ ሥልጣኑና አቅሙ ያላቸው ሁሉ ማድረግ ሳይችሉ ሲቀሩ፤ የተሻለ ዕውቀትና ግንዛቤ ያላቸው ሁሉ ጉዳዮችን በቸልተኝነትና በዋዛ ፈዛዛ ሲአልፉ፤ እጅግ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ የፍትሕ ድምፅ ሲታፈን-ሠይጣን አሸናፊ ሆኖ እንዲወጣ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል" ያሉት ለሁላችንም አስተማሪ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለዚህ የዘር ፖለቲካ የሚባለው ሰይጣን ጥርስ ስለዚህ የዘር ፖለቲካ የሚባለው ሰይጣን ጥርስ አውጥቶ ሳይናከስ፤ ገጀራና ጦር መዞ አማራን ከማጥፋቱ በፊት እኛ በውጭ የምንገኝ አማሮችና የሰበዊ መብት ተሟጋቾች የበኩላችንን ለማድረግ ተሰባስበን **"ዓለም አቀፍ የዓማራ ህብረትን"** ፈጥረናል።

የህብረቱ ዓላማም በመካሄድ ላይ ያለው ፀረ ዓማራ ዘመቻ ከዚህ በፊቱ ሁሉ ያሁን የባሰ በመሆኑ ያሁኑ ይባስ ብለን ልሳኑን ለተቀማው ዓማራ ልሳን ሁነን የዓማርውን ሰቆቃና ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለዓለም ህብረተሰብ ለማሰማት የተነሳሳን የዓማራ ወዳጆች ህብረት ነን። በውሸት ትርከት የዘር ፖለቲከኞችና ጽንፈኞች በአማራ ማህበረሰብ ላይ የሚዘሩትን የጥላችና የሃሰት ፕሮፖጋንዳ በሐቅና በአመክንዮ ለማክሸፍ፤ ሁሉም አደብ እንዲገዛ ለማድረግ፤ ተበታትነው የሚገኙ ለዓማራ ህልውና የሚታገሉ ድርጅቶችን ፤ ግለሰቦችንና የዓማራ ልሂቃንን በዝቅተኛ መስፈርት ስር አሰባስቦና አቀራርቦ በጋርና በመናበብ እየታገሉ ዓማራውን ከጭፍጨፋ እንዲታደጉ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ህብረቱን አቋቍመናል። ተመሳሳይ አመለካከት ባላቸውና በግል አነሳሽነት የተመሰረት ህብረት ነው። በህብረቱ የተሰባሰቡት ሁሉ ለግል ጥቅምና ዝና፤ ለስልጣንና ሃብት ለማፍራት የተሰባሰቡ እንዳልሆኑ ለማሳወቅ እንወዳለን።

እንዳለመታደል ሆኖ የህብረቱን መቋቋም ያልሆነ ስም ሰጠው ጥላሸት ሊቀቡ የሚሞክሩ መኖራቸውን ከምስረታው ጀምሮ ለመረዳት ችለናል። የጠቅላይ ሚንስትር ዓብይ ደጋፊዎች እንደሆንም አድርገው ሊፈርጁን ሞክረዋል። ሐቁ ግን ዶክተር ዓብይ ስልጣን ላይ እንደመጡ ሰፊ ድጋፍ ያገኙት ከዓማራው ሕዝብ እንደሆነ ይታወቃል። የዛሬ ዓመት ዋሽንግተን በሄዱበት ጊዜ በነቂስ ወጦ የተቀበላቸው አብዛኛው አማራው ዲያስፖራ እንጂ ኦሮሞው ትውልደ ኢትዮጵያዊ አልነበረም።

ባለው የዘር ፌድራሊዝም ኦሮሞ ሆነው የአማራውን ድጋፍ ያገኙበት ምስጢር ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ዓማራው በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ጽኑ እምነት ያለው፤ የጎሳ ፖለቲካ ስለሚጸየፍ የዓብይን ቃል አምኖ ደግፏቸዋል። ዓብይ በጥሩ አንደበታቸው ኢትዮጵያዊነትን አግዝፈው ተናግረዋል። የኢትዮጵያን ታላቅነት እያወደሱ ሃገሪቱ በጎሳ አትፈርስም፤ እንደ ሃገርም ትቀጥላለች፤ ወደ ታልቅነቷም ትመለሳለች ብለው ባደባባይ ሰብከዋል። ኢትዮጵያዊነትን፤ የኢትዮጵያን ክብር እና አንድነት የሚአስመልስለት መሪ ለሰላሳ ዓመት ሲናፍቅ የኖረው ዓማራ ተደሰተ፤ ደገፋቸውም፤ የጠቅላይ ምኒስትሩን አንደበትና ሃሳብ ወደደ፤ ቃላቸውን አመነ፤ ሊከተላቸውም ወሰነ። በኢትዮጵያዊነት በማመኑ ስለዓብይ የዘር ሃረግ ሳይጨነቅ ተከተላቸው። በዚህ ንግ ግራቸው ያልተመሰጠ፤ ያልተደሰተና ያልደገፋቸው አልነበረም። ያልተደስቱ ካሉ የዘር ፖለቲካ አራማጆች፤ ኢትዮጵያዊነት እንዲሰበክ ያልፈለጉና ጽንፈኖች ብቻ ነበሩ ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ህብረቱን የመሰረቱት ግለሰቦችም እንደማንኛውም ለኢትዮጵያ በጎ አሳቢ ኢትዮጵያዊዊ ሁሉ ወቃሾቻችን ጨምሮ ለአብይ ድጋፍ የሰጡ እንደነበሩ አይካድም። ይህ ደግሞ ሊአስወቅሰንና ፀረ ዓማራ ሊአሰኘን የሚገባ አይመስለንም። ዓብይ ቃላቸውን አጥፈው ሲገኙ አርሳቸውን ከመቃውም ወደኋላ የምንል ግን አይደለንም። በሰለጠነ አስተሳሰብና ፖለቲካ የሚአምን ሁሉ ማድረግ የሚገባው ይህንኑ ብለን እናምናለን።
በህብረቱ መመስረት ያልተደሰቱ ቢኖሩ አይደንቀንም። ሕብረቱን ለመቃወም ሲባል ብቻ ከንቱ አሉባልታ ለሚአወሩ፤ ተራ ስድብና እንካ ስላንትያ ወስጥ ገብተን እንድንተራመስ ለሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖች ግን ቦታን ጊዜ ሰጠን መነታረክ አንፈልግም። አስፈላጊም ሆኖ አላገኘነውም። ለዚህ ዓይነት የወረደ ንትርክ

የምናጠፋውን ጊዜ ለአማራው ሕዝብ ልሳን ሆነን ሰቆቅቃውንና ከፊቱ የተጋረጠውን የዘር ማጥፋት ዘምቻ ለመቃውም ማዋል አልብን ብለን እናምናለን። ስለዚህ ዓማራን ለመታደግ የተቋቋማችሁ ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና የዓማራ ልሂቃን ሁሉ ለአማራው ህልውና ስንል በአንድጥላ ስር ተሰባስበን በአንድነት ድማጻችንን እንድናሰማ ጥሪአችን በድጋሚ ይድረሳችሁ። በረባው ባረባው መነታረክ የሚበጀው ጠላትን ስለሆነ የህብረቱን ዓላም ዝቅ አድርገው በተራ እንካ ስልንታይ ንትርክ ሊአወርዱን ለሚፈልጉት ሁሉ እኛ ከፍ ባለ ሃሳብ ላይ ሆነን ምሳሌ ልንሆናቸው የገባል። አንድ ዓማራ ለሁሉም ዓማራ ሁሉም ዓማራ ለአንድ ዓማራና ለአንድ ኢትዮጵያ ይሁን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።